# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፡የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 26 ሕዳር 4 2001 ዓ.ም


## "ኢትዮጵያውን አንድ ሲሆኑ የመለስን አገዛዝ ማስወገድ ይችላሉ"

አና ጎሜዝ

ከዚህ በሁዋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ይኖራል ብየ አላምንም ያሉት ቀና ማሪያ ጎሜዝ፤ የመለስን አምባገነናዊ አገዛዝ ማስወገድ ከተፈለገ ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን በማቻቻል በአንድነት እንዲቆሙ ምክራቸውን አስተላለፉ።የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ አባልና በግንቦት 97 የኢትዮጵያ ምርጫ የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ የነበሩት አና ጎሜዝ ከጃማ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፤ የመለስ መንግስት በምርጫ የተሸነፈና የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁኝታ የሌለው እንደሆነ በ ዓይናቸው ዓይተው ማረጋገጣቸውን በማስታወስ፤ በጠመንጃ ሀይል ስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ለማስወገድ ፤የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሀይሎችልዩነታቸውን በዲሞክራሲያዊ መንገድ በማቻቻል ወደተቀናጀ የትግል መስመር መግባት እንዳለባቸው የሀገራቸውን ታሪክ ዋቢ በማድረግ ምክራቸውን አስተላልፈዋል።" ከኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ታጋዮች ጋር የወገናዊ ስሜት ስለሚሰማኝ ነው አንድነት እንደሚያስፈልግ ስናገር ቆየሁት" ያሉት ሚስስ ጎሜዝ፤" በኔ እምነት እንደዚህ ባለ ክፉ፣ እንኳን ኢትዮጵያን አብላጫውን የትግራይን ህዝብ በማይወክል መንግስት ከምትጨቆኑበት ምክንያቶች አንዱ በተለያየ ምክንያት ስለተከፋፈላችሁ ነው" ብለዋል።

እንደ ሚስስ ጎሜዝ ገለፃ፤ በዚህ ወቅት በተለያየ ርዕዮተ ዓለም፣ በዘርና በአንጃዎች መከፋፈል እጅግ የሚያሳዝን ነው። አና ጎሜዝ በማያያዝም፦" ኢትዮጵያውያን በአመለካከት፣ በአስተሳሰብና በዘር ምክንያት የሚመጡ ልዩነቶቻቸውን አልፈው አንድ ሲሆኑ፣ ዲሞክራሲያዊ ለሆነች ኢትዮጵያ ባንድነት ለመታገል ሲችሉ፣ የመለስን አገዛዝ ለማስወገድና ዴሞክራሲን ለማስፈን ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ" ብለዋል። ባራክ ኦባማ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው ከመመረጣቸው ጋር ተያይዞም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አምባገነኖች ባሉባቸው አገሮች የሚደረገው ዲሞክራሲን የማስፈን ትግል ለውጥ ያሳያል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል=ሚስስ ጎሜዝ። የኢትዮጵያውያኑን ትግል ምን ያህል ለመርዳት ዝግጁ እንደሆኑ የተጠየቁት አና ጎሜዝ፤ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ስላልሆኑ በዚህ ዙሪያ ድጋፍ ቢያደርጉም ድጋፉ ውስን እንደሚሆን፤ በ ኢትዮጵያ ለውጥ የማምጣቱ ትግል በዋነኝነት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተጣለ መሆኑን አስረድተዋል።ፕሬዚዳንት ኦባማ በበኩላቸው በዕጩነት ጊዜያቸው በተደጋጋሚ፦ "ስንጠብቅ የነበረው ራሳችንኑ ነው" በማለት፤ ለውጥ በዋነኝነት የሚመጣው በራስ ትግል እንደሆነ መናገራቸው ይታወሳል።ከክብርት አና ጎሜዝ ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የተከበሩ አና ጎሜዝ በአውሮፓ ፓርላማ የሶሻሊስት ቡድን አባል እና በ1997ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ ወቅት የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ቡድን ኃላፊ የነበሩ ሲሆን፤ በታዛቢነት ተግባራቸው በብዙ ተቃዋሚዎችና የዲሞክራሲ ደጋፊዎች ሲመሰገኑ በገዢው ፓርቲ ግን ወቀሳ ደርሶባቸዋል። ከየሮ (ጀማ ታይምስ) ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስለ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ወቅታዊ ሁኔታ፣ ስለ ኦነግ፣ ስለ አካባቢው መረጋጋት እና ስለ ግንቦት 7 ንቅናቄ ተነጋግረዋል።እኛም ይህን ቃለ ምልልስ በሁለት ክፍል በመክፈል በተከታታይ ሁለት ዕትማችን ለማቅረብ ፈልገናል። ለዛሬ ክፍል አንድ እነሆ፡=

**ጥያቄ፦** *የአውሮፓ ፓርላማ አባላት የዛሬ ሶስት አመት ገደማ ከምርጫው በኋላ 193 ሰላማዊ ሰልፈኞች በተገደሉበት ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ "የታለመ ማዕቀብ" እንዲጣል ጥሪ አቅርበው ነበር። የሕብረቱ ስራ አስፈፃሚ (የአውሮፓ ኮሚሽን) ይህንን ጥሪ እስከ ዛሬ የዘነጋው ለምንድን ነው?* *(ወደገጽ 4 ዞሯል)*

---

## ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ

## በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም

**ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ15350 ኪሎ ኸርዝ በ19 ሜትር ባንድ ወይም በ12120 ኪሎ ኸርዝ በ25 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ። ለወገኖቻችንም ይንገሩ።**

## ሞት አፋፍ ላይ የሚገኘው ፕሬስ ፤ቀብሩ በጥልቀት እየተማሰ ነው።አፋኙና ጨቋኙ የፕሬስ ህግ በፀደቀ ማግስት በጋዜጠኞች ላይ ዘመቻው ቀጥሏል።

የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ አሳታሚ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ እና ከፍተኛ አዘጋጁ ፍፁም ማሞለት ፤በትናንትናው ዕለት ህግን መቀለጃ ባደረገው፣በልማደኛውና በደነበረው የወያነ/ ኢ.ህአዴግ ዐቃቤ ህግ "ህዝብን በመንግስት ላይ የማነሳሳት " ክስ እንደተመሰረተባቸው ተገለፀ።የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዋነኛ መገለጫ የሆነውን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ተፈጥሯዊና ህጋዊ መብትን እንደ ጦር የሚፈራው አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ ፤ጋዜጠኞቹ ላይ ይህን ክስ የመሰረተው፤ የአንድነት ፓርቲ አመራር የሆኑትን የዶክተር ያዕቆብ ሀይለማርያምን ቃለ ምልልስ ፤እንዲሁም " ከአሜሪካ ምርጫ ምን እንማራለን?" በሚል ርዕስ የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ለቪ፣ ኦ፣ ኤ የአማርኛው ክፍል የሰጡትን አስተያዬት በጋዜጣቸው ላይ በመታተሙ ነው።

ዶክተር ያዕቆብ የቅንጅትን ስያሜ አስመልክቶ ቀደም ሲል ከአውራምባ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፤" ቅንጅት የተሰኘውን ውድ ስያሜያችንን ለማንም መንገደኛ ሰጡብን" ማለታቸውን ተከትሎ ፤ " ቅንጅት የሚለው ስያሜ ለኔ ተፈርዶልኛል" ብሎ ብቻውን የሚያወራው መንገደኛው አየለ ጫሚሶ " እንዴት ማንም መንገደኛ እባላለሁ?" በማለት፤ ክስ መመስረቱ ያታወሳል።
ብዙዎች የሞቱለትን፣ ሽህዎች የታሰሩለትንና ሚሊዮኖች መስዋዕት የከፈሉለትን ቅንጅትን ፤ያለ አንዳች የህሊና ማመዛዘን ለኔ ይገባኛል ያለውና ከመንገደኛም የወረደ የማንነት መገለጫ የሚገባው ይህ የወያነ/ ኢ.ህአዴግ እጅ ስራ የሆነው አየለ ጫሚሶ በጋዜጣው ላይ ክስ ሲመሰርት፤ በሌላ በኩል የአገዛዙ ደህንነቶች ወደ አውራምባ ታይምስ ቢሮ ስልክ በመደወል ፤ስለ ግንቦት ሰባት ንቅናቄ አንዳችም አይነት ፅሁፍ እንዳያትሙ ዛቻና ማስፈራሪያ መሰንዘራቸው ይታወሳል።
ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሰሞኑ የዓለማችን ታላቅ ክንውን የነበረውን የ አሜሪካ ምርጫ ተከትሎ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ መስራችና አመራር ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ከአሜሪካ ሬዲዮ የአማርኛው ክፍል በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት ፤ ስለአሜሪካ ምርጫ ያላቸውን አስተያዬት ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር በተብራራ መልኩ አስተያዬታቸውን ይሰጣሉ።በከትናንት በስቲያ ዕትሙ የአሜሪካን ምርጫ ከተለያዩ አቅጣጫ የዳሰሰው አውራምባ ታይምስ፤በዚሁ ጉዳይ ካቀረባቸው መጣጥፎች መካከል ዶክተር ብርሀኑ ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የሰጡት ቃለ ምልልስ አንዱ ነው።
የግንቦት ሰባት ጉዳይ ሲነሳ የሚይዙትን የሚጨብጡትን የሚያሳጣቸው መለስና አሸባሪ ግብረ አበሮቹ ፤ሀሳብን በነፃነት የመግለፅን መሰረታዊ እሳቤዎች በግላጭ በመጣስ ፤ በጋዜጣው አሳታሚ በዳዊት ከበደና በከፍተኛ አዘጋጁ በፍፁም ማሞለት ላይ ህዝብን በመንግስት ላይ የማነሳሳት የሚል ከዕውር አስተሳሰብ የመነጨ ዕውር ክስ መስርተዋል።"አየለ ጫሚሶ መንገደኛ መባሉ የትኛውን ህዝብ ነው በመንግስት ላይ ሊያነሳሳ የሚችለው?" በማለት ጥያቄ አዘል አስተያዬታቸውን የሰነዘሩ ወገኖች፤አንድ የፓርቲ አመራር የአሜሪካ ምርጫ ያስተላለፈለትን መልዕክት አስመልክቶ የሰጠውን አስተያዬት፤ ያውም በታዋቂ ሚዲያ የተላለፈን የግለሰብ ሀሳብ ማተም እንደ ወንጀል መቁጠር ፤ የአገዛዙን አምባገነንነት ብቻ ሳይሆን ገደል ጫፍ ላይ መድረሱን የሚያመለክት እንደሆነ አስረድተዋል።የህግን ልዕልና በመርገጥ ፤ በበሬ ወለደ ክስ ዕልፍ ዜጎችን ማስለቀስን አረመኔያዊ ድርጊት እንደ ሙያ የቆጠረው የመለስ አገዛዝ፤ በጋዜጠኞቹ ላይ ለመሰረተው ህዝብን በመንግስት ላይ የማነሳሳት ክስ የጠቀሳቸው አንቀፆች 240፣ 257 እና 261 ናቸው።
ከጥቂት ቀናት በፊት የዕምቢልታ ጋዜጣ፤ የቴወድሮስ ካሳሁንን ችሎት በዘገበበት ዕትሙ፤ ችሎቱን ያስቻሉትን ዳኛ የአባት ስም በመሳሳቱ የጋዜጣውን አሳታሚ ጋዜጠኛ ፅዮንን ጨምሮ አዘጋጆቹ ጋዜጠኛ ሀብቴ እና ጋዜጠኛ አጥናፉ መታሰራቸው ይታወሳል።በተለመደው የጋዜጠኝነት ሙያዊ አሰራር መሰረት በማረሚያ ሊስተካከል በሚገባው በዚህ ቀላል ጥፋት ምክንያት ሶስት ጋዜጠኞችን በማሰር ያልረካው ፀረ ዲሞክራሲው የፕሬስ ተቋማት አፍራሽ ግብረ ሀይል፤ በጋዜጣው ላይ የሁለት ሽህ ብር ቅጣት በመጣል አሳታሚዋን እንድትከፍል አድርጓል።ይህ የእስርና የገንዘብ ቅጣት በዕምቢልታ ጋዜጣ ላይ የተጣለው፤ ጋዜጣው ለተሰራው በጣም አነስተኛ ለሆነ ስህተት ማረሚያ እንዲያወጣ ባልተጠየቀበት ወይም ማረሚያ ለማውጣት ፈቃደኛ አይደለሁም ባላለበት ሁኔታ መሆኑ፤እርምጃው ምን ያህል ከክፋትና ከጠማማነት የመነጨ መሆኑን ያመለክታል ሲሉ ገዳዩን የተከታተሉ ወገኖች በወቅቱ አስተያዬታቸውን መስጠታቸው ይታወሳል።ከዚሁ ከቴወድሮስ ካሳሁን ችሎት ዘገባ ጋር በተያያዘ የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጅ፤ ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ ለእስር ተዳርጎ እንደነበር አይዘነጋም። (ወደገጽ 2 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## ወያኔ ተደናበረ እንደ ልማዱ?

ወያኔ ሰሞኑን በህጋዊነት ተመዝግበው ፓርላማ ውስጥ የተፈቀደላቸውን መቀመጫ የያዙ ፓርቲዎች አመራር አባላትና ሌሎች ኢትዮጵያውያንን በእስር ላይ ማዋሉ የኢትዮጵያ ዜና አውታሮች ዘግበዋል ። ከታሳሪዎቹም መሃል የኦፌዴን ዋና ፀሀፊ አቶ በቀለ ጅራታ እንሚገኙበትም ታውቋል ። ለጥቂት ሳምንታት ብቻ የሚሆን የዶላር ሪዘርቭ፤ እጅግ ያሻቀበ የዋጋ ንረት፤ ድርቅና ረሃብ፤ የነዳጅ እጥረት፤ ሽንፈት በሶማሊያ፣ ዴሞክራቲክ ምርጫ በልዕለ-ሃያል አሜሪካ ተደራርበው ወያኔን ቀልብ አሳጥተውታል ። በወራዳ እሽክርና ስልጣን ላይ መቆየት እችላለሁ የሚለው ስሌቱ የማይሰራ መስሎ እየታየው፣ በማ ብብት ውስጥ እንደሚወሸቅ ግራ ተጋብቷል ። የሰሞኑ የቻይና ህዛባዊ ሸንጎ ሊቀመንበር የው ባንጉም የአዲስ አበባ ጉብኝት ከዚሁ የወያኔ ምስቅልቅል ጋር የተያያዘ ይመስላል ።

ወያኔ የግንቦት 97 ምርጫን ውጤት አልቀበልም ብሎ የምዕራቦችን ተፅእኖ ለማላላት በተራ ሎሌነት ሱማሌን መውረር ብቻ ሳይሆን፤ ደቡብ ሱዳንንም ለማስገንጠል ሽብ ረብ ሲል መቆየቱ የታወቀ ነው ። ቻይናን ከደቡብ ብቻም ማስወጣት ሳይሆን፤ በሰብአዊ እርዳታ ከለላ የሰሜንና ምእራብ ሱዳን አሸማቂዎችንም በመርዳት፤ የጄኔራል አል በሺርን መንግስት በመጣል፤ ቻይናን ከሱዳን ነዳጅ ዘይት ተጠቃሚነት ለመንቀል በሚደረገው ሴራ ዋና ተዋናይ ሆኖ ሲያገለግልም ቆይቷል ። ሆኖም የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ሊያስከትል በሚችለው የፖሊሲ ለውጥ የተነሳ የተደናበረው የወያኔ መንጋ፤ በድብቅ ሲደጎመው የቆየው የፔንታጎን መቁነን ሊቋረጥ ይችላል ብሎ ስለሰጋና የሱማሌ አርበኞችንም ምትሃታዊ ጥቃት መቋቋም ስላቃተው፤ ከሱማሌ ለመውጣት ከመወሰኑም በላይ፤ የሎሌነቱን ተግባር ከምእራብ ወደ ምስራቅ ለማዞር የወሰነ ይመስላል ። በቻይና ጉያ ውስጥ ለመወሸቅ እየተርመሰመሰ ነው ማለት ማጋነን አይመስለንም ።

በዚህ ሁሉ መሃል ግራ የተጋባው መለስና ኩባንያው፤ የሱማሌ ሽሽቱንም ሆነ፤ የጌታ ለውጡን ለማድረግ፤ አባላቱንና ደጋፊዎቹን፣ ብሎም የኢትዮጵያን ህዝብም ማመስና ማተራመስ ፋታና ከለላ ይሰጠኛል ብሎ አስቧል ። የሰሞኑ እስርና የኢትዮጵያውያን ዜጎቻችን እንግልትም፣ ወያኔ እንደሚከሳቸው ኦነግ ስለሆኑ ወይም ከኤርትራ ስለሚገናኙ ሳይሆን፤ የወያኔ እንቅልፍ ማጣትና ፍርሃት የፈጠረው ነው ። የዛሬ ሶስት አመት፣ ወያኔ በህዝባዊ የተቃውሞ ማእበል በሰከረበት ወቅት፤ በሰላማውያን የቅንጅት መሪዎችና ደጋፊዎች ላይ ያደረገውን እመቃና ፍጅት ህዝብ የሚያውቀው በመሆኑ፤ የወያኔ ደንባራነትና ለከት የለሽ ፍርሀት ስለሚያስከትለው ጦስ ብንዘረዝር ለቀባሪው ማርዳት ይሆንብናል ። ወያኔ በፍርሃት በራደ ቁጥር፤ መዲናዋን በመትሮ ተኳሾች ይወርራል፤ ታክሲዎችን በፈንጂ ያጋያል፤ የትግራይ ቡና ቤቶችን በቦምብ ይደረምሳል፤ የራሱን ደጋፊ ጋዜጠኞች በጠራራ ፀሀይ ያስደበድባል ። የዘር ግጭት ይለኩሱልኛል ብሎ የሚያምንባቸውን ነገሮች ከማድረግ የሚቆጥበው አንዳችም የሞራል ለኮ የሌለው ወሮ በላ መሆኑን ፀሀይ ሞቀው ሃገር ያወቀው ነው ።

አንድ ቁም ነገር ተምረናል ። ወያኔ ተደናብሮ ዜጎቻችንን ባንገላታ ወይም በገደለ ቁጥር፤ ምን ወንጀል ተገኝቶባቸው ይሆን ብለን ላንጠይቅ ። የወንጀሎች ሁሉ መቀፍቀፊያ የሆነውን ዘረኝነትን መመሪያው ያደረገ ስርአት ፤ራሱን ላወጣው ህግ እንኳ ለማስገዛት ፈቃደኛ ባልሆነበት ሃገር ላይ የሚያፍንና የሚገድላቸው ፀሮቹ፣ በመሆኑም የህዝብ ወገኖች መሆናቸውን ለአፍታም አንጠራጠርም ። ወኔአቸውን ማድነቅ ፤ ቤተሰቦቻቸውን መርዳት፤ ከጎናቸው ቆሞ መታገል ነው ምርጫችን ።

## ሞት አፋፍ ላይ የሚገኘው ፕሬስ ከገጽ 1 የዞረ

ዓለማችን ፦" ውበታችን ልዩነታችን ነው" በሚል ዲሞክራሲያዊና ስልጡን አስተሳሰብ ልዩነትን እንደ አንድነት መሰረትና እንደውበት እየቆጠረች በምትገኝበት በአሁኑ ጊዜ፤ ከፕላኔታችን ጋር ፊፅሞ ሊራመድ ያልቻለው ወያነ/ኢህአዴግ ፤ "ሀሳባቸው ፤ከኔ አስተሳሰብ ጋር ተቃራኒ ነው የሚላቸውን ንፁህን ዜጎች በፈጠራ ክስ ከርቼሌ የመወርወርን አራዊታዊ ድርጊት፤ እንደ ጀግና ሙያ ባህል ማድረጉ፤በኢትዮጵያችን ዲሞክራሲን ለማስፈን በተለያዩ መንገድ እየታገሉ ያሉ ወገኖችን ለትግል ካነሳሳቸው ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ይታመናል።ዜጠኛ ዳዊት ከበደ፤ በተለይ በምርጫ 97 ወቅት ከፍተኛ አገራዊና ሙያዊ ሀላፊነታቸውን በብቃት ከተወጡት የፕሬስ ተቋማት መካከል የተወዳጇ ሐዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረ ሲሆን፤ የምርጫውን ቀውስ ተከትሎ በፈጠራ ክስ ከቅንጅት አመራሮች ጋር ለሁለት ዓመታት በእስር ካሳለፉት ጋዜጠኞች አንዱ ነው።

ዘግይቶ በደረሰን ዜና መሰረት በአውራምባ ታይምስ አሳታሚ በጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ እና በከፍተኛ አዘጋጁ በፍፁም ማሞለት የተመሰረተው የሀሰት ክስ፤ አብርሐም ተጠምቀ በተባለውና በዳኝነት ካባ ስር ተደብቆ የጥፋት ተልዕኮ ዋነኛ ደቀመዝሙርነቱን በአደባባይ ባስመሰከረው ካድሬ እንዲታይ ተደርጓል።ምንም ዓይነት የፍትህ ዕውቀትና ሽታ የማይታይበት ካድሬ አብርሐም ተጠምቀ፤ምርጫ 97 ትን ተከትሎ በቅንጅት አመራሮች፣ በጋዜጠኞችና በሲቪክ ማህበር መሪዎች ላይ ክስ የ አገዛዙ ወኪል ሆነው ክስ ከመሰረቱት ሶስት ዓቃቤ ህጎች አንዱ ሲሆን፤ በሁሉም ተከሳሾች ላይ የሞት ቅጣት እንዲበየን በግንባር ቀደምትነት ሽንጡን ይዞ የተከራከረ ጭፍን ካድሬ ነው።

ይህ ተላላኪ ካድሬ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የተሰጠውን የዐቃቤ ህግነት ካባ ወደ ዳኝነት እንዲቀይር ተደርጎ በ10ኛ ወንጀል ችሎት የግል ፕሬሶችን ጨርሶ ለማጥፋት ታስቦ በጋዜጦች ላይ በየምክንያቱ የሚፈበረኩትን ክሶች እንዲያይ መደረጉን የገለፁት ምንጬቻችን፤ ቀደም ሲል ያለ ጥፋታቸው የሞት ቅጣት እንዲበየንባቸው በዐቃቤ ህግ ካባ ስር የሞገታቸውን ጋዜጠኞች ዛሬ በዳኝነት ወንበር ሲያገኛቸው ምን ሊፈርድባቸው እንደሚችል መገመቱ ቀላል ነው ብለዋል።

## "ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ዉስጥ ነፃ ምርጫ ከገጽ 3 የዞረ

የጋራ የሆነ ነገር ያስፈልጋቸዋል፣ የጋራ ለሆነ ዓላማ ሊታገሉ ይገባል፤ ያም ዓላማ አንድ እና ዴሞክራሲያዊ የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር ነው። ይህ አውሮፓ እና በዚህም በአውሮፓ ፓርላማ ያሉ ሰዎች የሚደግፉት ነገር ነው፤ ነገር ግን እኛ ለዴሞክራሲ የሚታገሉትን የኢትዮጵያን ሕዝብና ድርጅቶች መተካት አንችልም።

**ጥያቄ፡** *አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች የኢትዮጵያ የግል መገናኛ ብዙሃን ብዙ እንቅፋቶች እንዳሉባቸው ይናገራሉ፤ በተለይም በቅርብ ጊዜ በመንግስት የተፈጠረው የፋይናንስ እንቅፋት አይነት። ከሁለት ዓመት በፊት በተደረገ ድንገተኛ የህትመት ዋጋ ጭማሪ ምክንያት ብዙ በገዢው ፓርቲ አባላት ያልተደገፉ ነፃ አጋዜጦች መውደቅ ጀመሩ። ከ97ቱ ምርጫ በኋላ በነፃ ጋዜጠኞች ላይ ከተደረገው ሰራትና እንግልት በተጨማሪ ፤በዚህ ዓመት የጸደቀው ህግ፤ መንግስት በፈለገው ጊዜ የታተሙ ጋዜጦች እንዳይከፋፈሉ እንዲያግድ ያስችለዋል፤ ይህንንም ሂስ ሰጪዎች አዲስ የአፈና ዘዴ እንደሆነ ይናገራሉ። የአውሮፓ ሕብረት የግል መገናኛ ብዙሃንን ለመርዳት የተለየ ዕቅድ ያለው ይመስሎታል?* **እና ጐሜዝ፡** ይሄ በእውነቱ ወሳኝ ጥያቄ ነው። ከሚያሳድዳቸው መንግስት የተነሳ ያን ያህል የግል ሚድያ በኢትዮጵያ ውስጥ የለንም። ይህ ደግሞ በተለያየ ደረጃ በኢትዮጵያ ሲከሰት አይተናል፤ በተለይም በዋናነት ከምርጫው በኋላ መንግስት ነፃ ፕሬስ አይፈቅድም። እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ አሁን ደግሞ ከምንም ግዜ በባሰ መንገድ እያሳደዷቸው ነው፤ በሌላ በሰለጠኑ መንገዶችም ህዝቡ መረጃን እንዳያገኝ እየከለከሉ ነው - በተለይም ከኢንተርኔት። ይህንንም ለማድረግ ከአንዳንድ መንግስታት፣ እንደተነገረኝ ከቻይና መንግስት፣ የሰለጠኑ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንኙነትን ለመዝጋት እርዳታ እያገኙ ነው፤ ይህንንም የሚያደርጉት ህዝቡ መረጃ ያገኛል ብለው ስለሚፈሩ ነው። ስለዚህም ይህ ትልቅ ጥያቄ ነው፤ የዴሞክራሲ ትልቅ ጥያቄ። እናም ከአውሮፓ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለመርዳት የሚደረጉ እርዳታዎች ነፃውን ሚዲያ የመርዳት ዓላማ እንዲኖራቸው እደግፋለሁ፤ እነዚህም ሚዲያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጪ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ የሚያስተላልፉ። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው። እኔ መላውን ኢትዮጵያ የሚያዳርስ ራዲዮ በጣም አስፈላጊ ነው እላለሁ። ራዲዮ ከየትም መተላለፍ ይችላል፤ በአማርኛ እና በሌላ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ደርሶ ይህንን ገዢው ፓርቲ ሊፈጥረው እየሞከረ ያለዉን የዝምታ እና የተዛባ መረጃ ግድግዳ እንዲሰብር። ይህ የአውሮፓ ሕብረት እና የአውሮፓ ፓርላማ ቅድሚያ ሰጥቶት ሊደግፈው የሚገባው ነገር ነው። በእውነት በኢትዮጵያ ዉስጥ ዴሞክራሲን ለማስፋፋት ከፈለግን፣ የመረጃን ነፃ ፍሰት መደገፍ አለብን። (ክፍል ሁለት ሳምንት ይቀጥላል)

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## ከህዝብ ጋር የመታረቂያው ጥሪ፤ ለመከላከያ አባላት

(ጽናት ፍቅሩ)

የወያኔን ባለስልጣናት መመሪያ በመቀበል በሶማሊያና በኦጋዴን **በረሀዎች እየወደቃችሁ** ለምትገኙ ፤ በኤርትራና በኢትዮጵያ ድንበር መካከል በሚገኙ ቋጥኞች ለመሸጋችሁ እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝብ ለዲሞክራሲና ለነጻነት የሚያደርገውን ትግል ለማፈን በቤተመንግስት ዙሪያ መሽጋችሁ ለምትገኙ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በሙሉ። ውድ ወገኖቼ፣ ዛሬ ማንነታችሁን የሚፈትን፣ ሰው መሆናችሁንና አለመሆናችሁን መለስ ብላችሁ የምታዩበትንና ለምን አላማ እንደተሰለፋችሁ እራሳችሁን የምትጠይቁበትን ትልቅ ጥያቄ ላቀርብላችሁ ወድጃለሁ። ጥያቄየም ግልጽና አጭር ነው። ለመሆኑ አገለግለዋለሁ ከምትሉት የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን እንደሚመስል አጢናችሁት ታውቃላችሁ? አጢናችሁት ከሆነ መልሳችሁን ምን ሆኖ አገኛችሁት? የኢትዮጵያ ህዝብ ይወዳችሁዋል ወይስ ይጠላችሁዋል? ይ ንቃችሁዋል ወይስ ያከብራችሁዋል? ይመርቃችሁዋል ወይስ ይረግማችሁዋል? ይቀርባችሁዋል ወይስ ይሸሻችሁዋል?

መልሳችሁ ምናልባት "አዎ ህዝባችን ይወደናል፣ ያከብረናል፣ ይመርቀናል፣ ይቀርበናል" የሚል ከሆነ እንደገና እረሳችሁን መለስ ብላችሁ እንድታዩ እጋብዛለሁ ነገር ግን መልሳችሁ ህዝብ ይጠላናል፣ ይነቀናል፣ ይረግመናል፣ ይሸሸናል የሚል ከሆነ አዎ አልተሳሳታችሁም እላችሁዋለሁ። አትገረሙ፣ ዋናው ችግር ዛሬ በህዝብ መጠላታችሁ አይደለም ፤ ጥቂቶች በሰሩት ጥፋት በጅምላ ልትጠሉ የምትችሉበት አጋጣሚ ሰፊ ነውና። ህዝብ የእያንዳንዱን ወታደር አስተዋጽዎ፣ አቋምና አስተሳሰብ ምን እንደሚመስል አይመረምርም። ይህ ማለት ግን ህዝቡ በአጠቃላይ ስለ ወታደሩ ባህሪ መናገር አይችልም ማለት አይደለም። ስለያንዳንዱ ወታደር ማንነት አያውቅም ማለት ስለአጠቃላዩ ወታደር አያውቅም ማለትም አይደለም። ስለ ወታደር ወረታው ማንነት በተናጠል መናገር ባይችል፣ የኢትዮጵያ ወታደር ገዳይ ነው ወይም ህዝባዊ ነው ብሎ በጅምላ መናገር ይችላል። አሁንም እንዳልኳችሁ ዋናው ክፋት በህዝብ መጠላታችሁ አይደለም። ዋናው ክፋት ህዝብ ለምን እንደሚጠላችሁ የማታውቁ ከሆንና አውቃችሁም ለማሻሻል ሙከራ የማታደርጉ ከሆን ነው።

የኢትዮጵያ ወታደር በህዝብ የተጠላው ወታደር ስለሆነ ወይም የኢትዮጵያ ልጅ ስላልሆነ ወይም ውትድርና መጥፎ ስራ ስለሆነ አይደለም።ውትድርና በጣም የተከበረ፣ ስራ ነው።ውትድርና የሚያሸልም የሚያስከብር ስራ ነው። ለወታደር የሚሰጠው ክብር በሰለጠኑት እና ባልሰለጠኑት አገሮች መካከል የመጠን ልዩነት ቢኖረውም ፣ ክብሩ ግን እንዳለ ነው። በሰለጠኑት አገሮች ያለው ወታደር ተልእኮው ግልጽ ነው።ለአገሩ ጥቅምና ደህንነት ሲል ተልእኮውን ይፈጽማል። ለፕሬዝዳንቱ ወይም ለንጉሱ ስልጣንና እድሜ ሲል አይዋጋም። የፕሬዝዳንቱን ተቃዋሚ ግደል ተብሎ በፕሬዝዳንቱ ቢታዘዝ አሻፈረኝ ይላል። ፕሬዝዳንት ቡሽ አንዱን የአሜሪካ ወታደር ጠርቶ ኦባማን ግደለው ቢለው ያወታደር ፕሬዝዳንቱን ዞር በል ነው የሚለው።ያልሰለጡ አገሮች ወታደሮች ግን ይህን ከመፈጸም ወደሁዋላ አይሉም። ኦባማ ኢትዮጵያዊ ቢሆንና መለስ ለወታደሩ ግደሉት ብሎ ትእዛዝ ቢሰጥ የኢትዮጵያ ወታደር ቃታ ከመሳብ አይመለስም። የሰለጠነ አገር ወታደር የራሱን ዜጋ ቀርቶ ውሻ እንኳን አይገድልም። የደሀ አገር ወታደር ግን ህጻናትን ሳይቀር ከመግደል አይመለስም። የጠቅላይ ሚኒስትሩን ወይም የፕሬዝዳንቱን በስልጣን ላይ የመቆየት እድሜ ያህጻን ልጅ የሚፈታተን ከሆነ ከመገደል አያመልጥም። በጥቅምት 22 1998 ያየነውም ይህን ነበር።

ከጥቅምት 22 በፊትና በሁዋላ ወታደሩ ንጹሀን ዜጎችን እየገደለ ያለው አምባገነኑ መለስ በስልጣን ላይ ለዘላለም እንዲቆይ ለማድረግ ነው። የኢትዮጵያ ወታደር የሚጠላውም በዋናነት ለዚህ ነው። የወታደር ስነምግባሩን አውልቆ ጥሎ ፣ የጥቂቶች ባሪያና ሎሌ ስለሆነ ነው። አሁን ያለው ወታደር፣ በእነመለስ ዜናዊ እንደፈለገ የሚሽከረከር፣ ግደል ሲባል የሚገድል፣ ውረር ሲባል የሚወር፣ ለምን ብሎ ለመጠየቅ የማይችል ከሰው በታች ከእንስሳ በላይ የሆነ ወታደር ነው። ሀይሉና ወኔው በውጭ ጠላት ላይ ሳይሆን በሲቪሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚታይ ስለሆነ ነው።

ጥቅምት 22፣ 1998 ተነስቶ የነበረውን ህዝባዊ አመጽ የቀለበሰው የጥቂቶች ባሪያና አገልጋይ የሆነው ይህ ወታደር ነው። ይህ የመለስ ወታደር በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ወንድሞቹን፣ እህቶቹን፣ እናቶቹንና አባቶቹን ገድሏል። ከማን እንደተወለደ ፣ ለማን እንደቆመ፣ በማን ወዝ እንደሚያድር እረስቶ እየመገበው ያለውን እጅ ቆርጧል። በወለደው፣ በሚያበላውና በሚያጠጣው ህዝብ ላይ ቃታውን ስቧል። ዛሬ ይህ ጭፍን ወታደር በወሰደው እርምጃ አገራችን ዲሞክራሲንና እድገትን እንዳትላበስ፣ በጥቂት ወሮበሎች እንድትተዳደርና ሀብት ንብረቷ እንዲዘረፍ ሆኗል። ወታደሩ እጅግ የሚጠላውም ለዚህ ነው።

የኢትዮጵያ ወታደር በሶማሊያ በረሀ ሄዶ ሲቃጠል ማንም ኢትዮጵያዊ ደረቱን አልደቃም፣ እንባ አላፈሰሰም። በተገላቢጦሹ " ሶማሌ ከዳር እኛ ከመሀል" እየተባለ ነው የተዘመረው፤ ሆዳም፣ ሌባና ማህይም እየተባለ ነው የተሰደበው።

በርግጥ እያንዳንዱ ወታደር የመለስ ባሪያ አይደለም። ጀግናና ህዝባዊ ወታደሮች እንዳሉ አውቃለሁ። ነገር ግን እራሳቸውን እስካልለዩ ድረስ የኢትዮጵያ ወታደር በሚለው ስም አብረው መፈረጃቸው አያቆምም። ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት ህዝብ በጅምላ እንጅ በተናጠል አይፈርጅም።እያንዳንዱ ወታደር በጅምላ እንዳይጠላና እንዳይወቀስ ከፈለገ በቅድሚያ እራሱን ማግለል ፣ ጥቂት አምባገነን መሪዎችን በመቃወም መጀመር አለበት። ለእነመለስ ዜናዊ አልሞትም አልገድልም፣ ለህዝብ ጥቅም እሞታለሁ እገድላለሁ ብሎ መነሳት አለበት። ያንጊዜ እራሱንም አገሩንም ነጻ ያወጣል። ክብሩን ከወደቀበት አቧራ ላይ አንስቶ እንደገና ይለብሳል። የኢትዮጵያ ወታደር የመጥፎ ድርጊት ምሳሌ ከመሆን ወጥቶ የጥሩ ነገር ምሳሌ ለመሆን እንደሚበቃ አምናለሁ።

**የመጨረሻው** መልእክቴም ይህንኑ አጠንክሬ መናገር ነው። ከህዝብ ጋር ያላችሁን ግንኙነት መርምሩና ዛሬውኑ እርምጃ ውሰዱ። ክብራችሁ ይመለስሳል፣ ዝናችሁይታደሳል። ከሁሉም በላይ ሰው ትሆናላችሁ። በድል እንገናኝ።

---

**"ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ "**ከገጽ 4 የዞረ

**እና ጐሜዝ፡ እንግዲህ ከምርጫው በፊት ተስፋዎች ነበሩኝ፣ ኢትዮጵያውያን ወጥተው በምርጫው እንዲሳተፉ፤ ይህንንም ዕድል በመጠቀም ያላቸዉን ፈቃደኝነት፣ ዝግጁነት እና ለዴሞክራሲ ያላቸውን እምነት እንዲያሳዩ ነበር፤ ያም ተሳክቷል። ህዝቡም አስደናቂ ነበር፤ ያንንም በግልጽ ተወጥቶታል። በዛን ጊዜ ያንን የተናገርኩት፣ አንዳንድ የተቃዋሚ ቡድኖች ምርጫው ገና ሳይከሰት ውጤቱን በመፈታተን ላይ መሆናቸው ስላሰጋኝ ነበር። እንደሚመስለኝ ይህ የተፈጠረው ቀድሞ ከነበሩና መኖርም ከነበረባቸው ጥርጣሬዎች ጋር ተያይዞ ነው። ቀድሞውኑ ፍርሃት ነበረባቸው፤ አገዛዙ የምርጫውን ውጤት እንደሚያዛባ ነግረውኝ ነበር። ውጤቶቹ ከታወቁ በኋላ፣ በተለይም የአዲስ አበባው ውጤት ከታወቀ በኋላ፣ ነበር በሌሎች ቦታዎች የነበሩትን ውጤቶች ማዛባት የጀመሩት። ውጤቱን የማዛባቱን ተግባር የተያያዘው መንግስት እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ነገር ግን ህዝቡ ፍላጎቱን ለመግለጽ እና ወጥቶ ለመምረጥ እድል ማግኘቱ አስፈላጊ ነበር። ምንም እንኳ ኋላ ላይ የምርጫው ውጤት ተቀይሮ ለዴሞክራሲ የነበረው ተስፋ ቢዘጋም፣ አገዛዙ የህዝብን ፍላጎት ለመቀልበስ የምርጫውን ውጤት ለማዛባት መገደዱ ለርሱ መጥፎ ነው ብዬ አምናለሁ። በዛን እለት የህዝቡ ፍላጎት በታላቅ ሁኔታ ተገልጿል፤ መንግስት ሊደብቀው ያልቻለው አንድ ውጤት ነበረ - ያም የአዲስ አበባ ውጤት ነው። የአዲስ አበባ ውጤት ደግሞ፣ ከቦታ ቦታ ካሉ የተወሰኑ ልዮነቶች በስተቀር፣ ባገሪቱ ዙሪያ የነበረውን ውጤት የሚያንጸባርቅ ውጤት ነው። እናም በኔ አመለካከት፣ ያንን ጥሪ ያስተላለፍኩት ለዚህ ነው - ተቃዋሚዎች ህዝቡን ተስፋ የሚያስቆርጥና ለምርጫ እንዳይወጣ የሚከለክል መልዕክት እንዳያስተላልፉ። በስተመጨረሻ፣ ህዝቡ ሊመርጥ ወጣ። ለኔ ይህ በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል። መለስ ህዝቡ ለዴሞክራሲ ዝግጁ አይደለም ብሎ ሊናገር አይችልም። የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ዝግጁ ነው፣ ዴሞክራሲን ይፈልጋል፤ ይህንንም በታላቅ ቁጥር ለምርጫ በመውጣት አሳይቷል።**

**ጥያቄ፡** *አንዳንድ ሂስ አቅራቢዎች ሲናገሩ፣ ኢትዮጵያውያን በ97ቱ ምርጫ ወቅት "ከሁለት ክፉዎች የተሻለውን" ነበር የመረጡት፣ እንዲሁም ደግሞ ነፃ ምርጫ እና ፍትሓዊ ቆጠራ ቢደረግም እንኳ ኦነግ እስካልተሳተፈ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ ለውጥ አይኖርም ይላሉ። በአውሮፓ ፓርላማ በኩል ኦነግን ወደፊት በሚደረጉ ምርጫዎች ለማሳተፍ እና ለዛም የሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ሙከራ አለ ወይ?*

**እና ጐሜዝ፡ እኔ ያንን አላምንም...ፍትሓዊ ቆጠራ ተካሂዶ ቢሆን ኖሮ፣ በርግጥም ያ በኢትዮጵያ ትልቅ ለውጥ ያመጣ ነበር። የተለየ መንግስት፣ እንደውም በስምምነት ኢህአዴግን ራሱን ያካተተ መንግስት። ነገር ግን የተለየ መንግስት እና የተለየ ፓርላማ። ይህ አዲስ መንግስት ደግሞ፣ አሁን ባለው ምንግስት ፖሊሲዎች ምክንያት ከፖለቲካው መድረክ ውጪ ላሉት፣ ለተገፉት፣ እንደ ኦሮሞ ነፃነር ግንባር (ኦነግ) ላሉት ድርጅቶች እጁን ይዘረጋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በኔ እምነት ይህ ሁኔታዉን ይለውጠው ነበር። ነገር ግን ምርጫው ተዛብቷል፤ በኢትዮጵያ ውስጥም ዴሞክራሲ የለም። ምርጫውን የሰረቀና የኢትዮጵያን ህዝብ እየጨቆነ ያለ አገዛዝ ነው ያለው። ስለዚህ እኔን እንደሚመስለኝ፣ ኦነግ እና ሌሎች ድርጅቶች፣ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም አገር ውስጥ ወይም ውጪ ሃገር ሆነው ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ከሚታገሉት ጋር አንድ ላይ መሰባሰብ አለባቸው። ፣**

*ወደገጽ 2 ዞሯል*

# ሃይለ ሀሳብ

## “ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ይኖራል ብዬ አላምንም” አና ማሪያ ጎሜዝ

**አና ጐሜዝ፡** እኔ እንደሚመስለኝ፥ መጀመሪያ ላይ ኮሚሽኑ ይህንን ጥሪ አልዘነጋውም። ለኢትዮጵያ እርዳታ የሚሰጥበትን መንገድ ቀይረውት ነበር። ነገር ግን፣ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ነገሩ ሁሉ ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ ተመልሷል። እንደውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጠው እርዳታ ጨምሯል፤ ይህ መንግስት ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት እንደበደለ እናውቃለን፤ ምክንያቱም አገሪቱ በገዢው ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥር ስር ነው ያለችው። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት፥ በአውሮፓ ኮሚሽን ውስጥ፣ ወይም በአውሮፓ መንግስት ውስጥ፣ ኢትዮጵያን በተመለከተ ብዙ ግብዝነት ሰላለ ነው። በተለይም በአፍሪካ ውስጥ ዲሞክራሲን እና የሰብዓዊ መብቶችን በማስፋፋት ረገድ የአውሮፓ እምነቶችና አላማዎች ምንድን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ጽኑ የሆነ ወይም አንድ ወጥ የሆነ መልስ የለም። ይህም የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ይጐዳል። ከዚያም አልፎ አውሮፓ በኢትዮጵያውያን እንዲሁም በአጠቃላይ በአፍሪካውያን አይን የምትታይበትን መንገድ ይጎዳል፤ ይህም እኔን እጅግ ይጸጽተኛል።

***ጥያቄ፡*** *ታዲያ ይህ [የአውሮፓ ግብዝነት] በዓለም ዙሪያ ይታይ የለ እንዴ? ለምሳሌ፥ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች ብዙ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ስለሚካሄዱባት፤ ነገር ግን ከምዕራባውያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሰላላት ስለ ሳውዲ አረቢያ ይናገራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ዝምባብዌ ሰላለው ችግር እናውቃለን፤ ከሱ የበለጠ አፋኝ የሆኑ፣ ምርጫ የማያካሂዱ ወይም ካካሄዱም የሚሰርቁ፣ እንዲሁም ብዙዎችን የሚገሉ የአፍሪካ መንግስታት እያሉ ሙጋቤ በምዕራባውያን በኩል ከፍተኛ ግፊት ይደረግበታል። ታዲያ ይሄ [ግብዝነት] እየተስፋፋ አይደለም ወይ?*

**አና ጐሜዝ፡** አዎን ነው። በተጨማሪም፥ የሰብዓዊ መብቶች የቡሽ መንግስት እና የአውሮፓ መንግስታትና ተቋማቶች ድክመት ተበዳዮች መሆናቸውን ነው። ይህ ከዓለም አቀፍ ህግና ከሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ መንገድ የወጣ ነው። ለዚህም ነው አንተ የጠቀስካቸውን አይነት እና በኢትዮጵያ ላይ እየተወሰዱ ያሉትን አይነት <u>የአቋም ጽናት የጎደላቸው</u> ሁኔታዎች የምናየው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ግልጥ ብሎ የታየው በሆካይዶ [ጃፓን] በተካሄደው የቡድን 8 አገሮች ስብሰባ ላይ ነው። በዛ ብዙ የአውሮፓ መሪዎች በነበሩበት ስብሰባ ላይ በዚምባብዌ ላይ ማዕቀብ እንዲጣልባት ጥሪ ያደርጉ ነበር፤ በነገራችን ላይ በዚምባብዌ ለውጥን ለማምጣትና የሙጋቤን አምባገነናዊ መንግስት ለማብቃት ያ ጥሪ አስፈላጊም ነው፤ መደረግም ነበረበት። ነገር ግን፣ እንዲያ እያደረጉ በነበረበት ሰዓት፤ የተከበረ የዓለም ወይም የአፍሪካ መሪ ይመስል፤ መለስ ዜናዊን ሲያስተናግዱት ነበር። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሆንም፣ <u>ስልጣኑ ከህዝብ የተገኘ እንዳልሆነ</u> በ1997ቱ ምርጫ ወቅት አይቻለሁ። እናም፣ በህዝቡ ያልተመረጠ አምባገነን እንደመሆኑ መጠን፤ በተጨማሪም ሶማሊያን ስለወረረ፤ በዓለም መንግስታት ሊሸለም አይገባውም። እና እውነት ነው፣ <u>ይህ መዋዠቅ እና የዓላማ ጽናት ማነስ</u> በዓለም ላይ በግልጽ አለ።

***ጥያቄ፡*** *ባጠቃላይ፣ ባለፉት ሶስት አመታት የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሁኔታ፤ ወይም ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ጉዞ፤ ተሻሽሏል ወይስ ቁልቁል ወርዷል?*

**አና ጐሜዝ፡** ባጠቃላይ በዓለም ላይ የተለያዩ ነገሮችን ታያለህ፤ በኢትዮጵያ ግን በጭራሽ አልተሻሻለም። ባንድ በኩል፥ ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲን ይፈልጋሉ፣ ለለውጥም እጃቸውን ዘርግተዋል፤ በምርጫ 97ም በሰላም ተሳትፈዋል። ነገር ግን ያ ተስፋቸው በመለስ ዜናዊ አገዛዝ እና በአፈናው ተሰበረ። እናም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ በጭራሽ አልተሻሻለም። የዓለም መንግስታትም ለዚህ ሃላፊነት አለባቸው፤ ምክንያቱም የመለስ ዜናዊን አይነት መንግስት እየረዱ ነው። ይህ ግን የዴሞክራሲ ታጋዮችን ተስፋ እንዲቆርጡና ስራቸውን እንዲተው በቂ ምክንያት አይደለም። ይልቁንስ ጥረታችንን በእጥፍ ድርብ እንድንጨምር ምክንያት ነው። በተጨማሪም፥ የቡሽን መንግስት ፍፃሜ በመጨረሻ ስለምናይና የአፍሪካ ዘር ባላቸው በፕሬዘዳንት ኦባማ ስር አዲስን ዘመን ስለምናይ ነው። ይህ ሲሆንም፥ ዴሞክራሲን እና የሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ በአሜሪካ ለውጥ እንደምናይ እርግጥ ነው።

***ጥያቄ፡*** *የቡሽ አስተዳደር ከመጀመሩ በፊት፣ የሱ ባለሰልጣናት መረጋጋትን ከዴሞክራሲ እንደማያስቀድሙ አውጀው ነበር። ነገር ግን ብዙ ተመልካቾች እና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች የቡሽ አስተዳደር ታቃራኒውን እንዳደረገ ነው የሚናገሩት። እና እርሶ ከኦባማ ለውጥ ይጠብቃሉ?ከሆነስ ምን ያህል ለውጥ?*

**አና ጐሜዝ፡** እንደሚመስለኝ፥ ማንኛውም ተወዳዳሪ ምርጫውን ቢያሸንፈውም፣ ለዓለም ህዝብ ብዙ ሃዘን ያመጣውን የቡሽን አስተዳደር መጨረሻ ነው የምናየው። በርግጥም ይህ ለውጥ አሸናፊው ኦባማ ቢሆን የበለጠ ይደምቃል፤ አደርጋቸዋለሁ ብሎ ቃል ከገባቸው ነገሮችና እሱና ወክሎት የሚወዳደረው የዴሞክራቲክ ፓርቲ ከሚያምኑባቸው ነገሮች አኳያ። በኔ እምነት፥ የኦባማ የግል ባህሪ፣ የአፍሪካ ዝርያ መሆኑ እና በተለያዩ የዓለም ሃገራት፣ በተለይም እንደ ኢንዶኔዥያ ባሉ ሃገሮች፣ ማደጉ ፤አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋን ባፋጣኝ ለዉጣ ከመረጋጋት ይልቅ ዴሞክራሲን፣ ሰብዓዊ መብቶችንና ፍትህን ማስቀደም እንዳለባት ከሌሎች ይልቅ በተሻለ እንዲረዳ የሚያደርገው ይመስለኛል።

***ጥያቄ፡*** *በተለያዩ መድረኮች ላይ ተቃዋሚዎች ገዢውን ፓርቲ ለመታገል አንድነት እንዲፈጥሩ ሲመክሩ ቢከርሙም፣ ያ ግን የሚከሰት አይመስልም። ሕብረት፣ ኦፌዴን እና ኢዴአፓ የተባሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፓርላማ የገቡ ሲሆን፤ የቀድሞው ቅንጅት አመራር አባላት ደግሞ ስማቸውን ወደ አንድነት - አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ - ለውጠዋል። የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ከምርጫዎቹ ውጪ ቀርቷል። እንደገና ደግሞ የቀድሞው ቅንጅት በኢንጂነር ሃይሉ ሻወል እና በአየለ ጫሚሶ በሚመሩ በተጨማሪ አንጃዎች መከፋፈሉ ይነገራል። አንዳንድ ተቃዋሚዎች ደግሞ ከኤርትራ መንግስት ጋር እየሰሩ ነው፤ ይህም ባሁኑ ሰዓት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በጦርነት ላይ የሚገኘውን የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን (ኦብነግ) ያካትታል። ተቃዋሚዎች በአንድነት እንዲሰሩ ለማድረግ አሁን ምን በማድረግ ላይ ይገኛሉ?*

**አና ጐሜዝ፡** ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ዴሞክራሲን ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት ለመደገፍ እችላለሁ፣ እደግፋለሁም። ነገር ግን እኔ ኢትዮጵያዊት ዜጋ አይደለሁም። ኢትዮጵያ የምትፈልገውን ለዉጥ ደግሞ ማንም ሰው ከውጪ ሊያመጣው አይችልም። ይህ የኢትዮጵያውያን የራሳቸው ስራ ነው። ውጪ ያሉት ሰዎች መንግስታቶቻቸዉን፣ ለምሳሌ የአውሮፓን ሕብረት መንግስት፣ ኮሚሺኑን፣ ሃላፊነቱን በማስታወስ ሊረዱ ይችላሉ። ነገር ግን ይህም ቢሆን የተወሰነ ሃላፊነት ነው፤ ምክንያቱም ዋናው ሃላፊነት ያለው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ነው። ለዚህም ነው፤ በኢትዮጵያ ካሉ የዴሞክራሲ ታጋዮች ጋር የወገናዊነት ስሜት ስለሚሰማኝ ነው፣ አንድነት እንደሚያስፈልግ ስናገር የቆየሁት። በኔ እምነት፥ እንደዚህ ባለ ክፉ፤ እንኳን ኢትዮጵያን አብላጫውን የትግራይን ህዝብ እንኳ በማይወክል መንግስት ከምትጨቆኑበት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ ምክንያቶች ስለተከፋፈለ ነው። በዘር፣ በርዕዮተ አለም እና በተለያዩ አጀንዳዎች። ያ ደግሞ የሚያሳዝን ነው። ኢትዮጵያዎያን ባመለካከት፣ ባስተሳሰብና በዘር ምክንያት የሚመጡ ልዩነቶቻቸውን አልፈው አንድ ሲሆኑ፣ ዲሞክራሲያዊ ለሆነች ኢትዮጵያ ባንድነት ለመታገል ሲችሉ፣ የመለስን አገዛዝ ለማስወገድና ዴሞክራሲን ለማስፈን ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ። በልዩነታቸው ከቀጠሉ፥ አንዳንዶች ስለ አማራ የበላይነት እየሰበኩ፣ ሌሎች ደግሞ ከኦሮሞ ህዝብ የቁጥር ብዛት የሚመጣን ፍርሃት እያፋፉሙ፤ ዲሞክራሲያዊት የሆነች ኢትዮጵያን ለመገንባት ባንድ የጋራ ዓላማ ላይ ካልተቀራረኑ፤ በእርግጥም ያ፣ ይህ አምባገነናዊ መንግስት እንዲቀጥል የሚፈቅድ ጥሩ ዘዴ ነው።

***ጥያቄ፡*** *ከ97ቱ ምርጫ በፊት በመጋቢት ወር አይሪን ለተባለው የተባበሩት መንግስታት የዜና አውታር በሰጡት ቃለ ምልልስ፣ “ሁሉም ፓርቲዎች የደጋፊዎቻቸውን ተስፋ እና ስሜት ለማርገብ እና ሁሉም ከምርጫው በኋላ ውጤቱን <u>በጸጋ</u> እንዲቀበሉት ለማድረግ እንደሚጥሩ ተስፋ አለኝ” ብለው ነበር። ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ገዢው ፓርቲ ይህ እርሶ ተስፋ ያደረጉትን በስኬታማነት ተወጥተውታል?*

*፤ወደገጽ 3 ዞሯል*